መልእክት አራት

## አንበሳው-በግ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ ራእ. 5፥5-10

I. **የራእይ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስ ስእል ነው፤ የዚህ መጽሐፍ ሃያ ሁለት ምዕራፎች ኢየሱስን የሚያሳዩና የሚገልጹ አንድ ስእል ናቸው—1፥1-2፤ 5።**

II. **"እነሆ ከይሁዳ ነገድ የሆነው አንበሳ እርሱም የዳዊት ሥር...ድል ነሥቷል"—5፥5፦**

ሀ. በዘፍጥረት 49፥8-9 እንደተገለጠው አንበሳ ጠላትን እንደሚዋጋ ጠንካራ ተዋጊ ክርስቶስን በስእል የሚያሳይ የእርሱ ምልክት ነው።

ለ. የክርስቶስ ድል መንግሥት መጽሐፉን እና ሰባት ማኅተሞቹን ለመዘርጋት ብቁ ያደርገዋል—ራእ. 5፥5-10።

ሐ. *የዳዊት ሥር* የሚለው ስያሜ ክርስቶስ የዳዊት ምንጭ እንደሆነ ያመለክታል፤ ስለዚህ፣ በዘር ሃረጉ ውስጥ የክርስቶስ የቀደመው አባት የሆነው ዳዊት፣ ክርስቶስን "ጌታ" ብሎ ጠርቶታል—ማቴ. 22፥42-45።

መ. ከይሁዳ ነገድ እንደሆነው አንበሳ፣ ክርስቶስ የእግዚአብሔርን ጠላት የሆነውን ዓመጸኛው ሰይጣንን አሸንፎታል፣ ድል ነሥቶትማል፣ እንደ የሚቤዠው በግ፣ የወደቀውን ሰው ኃጢአት አስወግዷል፦

1. እንዲህ በማድረግ፣ ለእግዚአብሔር አላማ መፈጸም እንቅፋት የሆኑትን አስወግዷል።
2. ውጤቱም የእግዚአብሔርን ኢኮኖሚ የተመለከተውን መጽሐፍ ለመዘርጋት የተገባው መሆኑ ነው።

III. **"በዙፋኑና...መካከል እንደ ታረደ በግ ቆሞ አየሁ፣ ሰባትም ቀንዶችና ሰባት ዓይኖች ነበሩት እነርሱም ወደ ምድር ሁሉ የተላኩ የእግዚአብሔር መናፍስት ናቸው"—ራእ. 5፥6፤ 1፥4፤ 3፥1፦**

ሀ. ምእራፍ አምስት ላይ ክርስቶስ ወደዚያ ከዐረገ በኋላ በሰማያት ያለው ትእይንት አለ፦

1. ለሐዋርያው ዮሐንስ ከይሁዳ ነገድ እንደሆነው አንበሳ ተጠቀሰ፣ ለዮሐንስ ግን የታየው እንደ በግ ነበር።
2. እንደ አንበሳ፣ ጠላትን የሚዋጋ ተዋጊ ነው፤ እንደ በግ፣ ለእኛ ቤዛችን ነው።
3. እኛን ለመቤዠት ተዋጋ፣ ከጠላት ጋር ያለውን ውጊያ አሸነፈ፣ ለእኛም ቤዛነትን ፈጸመ።
4. ለጠላት አንበሳ ነው፣ ለእኛ በግ ነው፤ ስለዚህ እርሱ አንበሳው-በግ ነው።

ለ. ቤዛነትን በተመለከተ፣ ከዕርገቱ በኋላ ክርስቶስ በሰማያት በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጧል (ዕብ. 1፥3፤ 10፥12)፣ የእግዚአብሔርን አስተዳደር ማከናወንን በተመለከተ ደግሞ፣ በዕርገቱ አሁንም ቆሟል።

ሐ. *እንደ ታረደ* የሚለው ቃል የሚያመለክተው በጉ አሁን እንደ ታረደ እና በራእይ 5 የታየው በሰማያት ያለው ትእይንት የተካሄደው ክርስቶስ ወደ ሰማይ ከዐረገ በኋላ ወዲያውኑ መሆኑን ነው።

መ. ጌታ ሰባት ቀንዶች አሉት—ቁ. 6፦

1. ቀንዶች ለመዋጋት የሚሆን ጥንካሬ ያመለክታሉ—ዘዳ. 33፥17።
2. ክርስቶስ የሚቤዠው በግ ነው፣ ሆኖም ለመዋጋት ቀንዶች አሉት።
3. እርሱ የሚዋጋው ቤዛ ነው፤ በሰባት ቁጥር እንደተመለከተው በእግዚአብሔር እንቅስቃሴ ውስጥ መዋጋቱ ተጠናቋል።

ሠ. ዓይኖች ለማስተዋልና ለመመርመር ናቸው፦

1. እንደ የሚቤዠው በግ ክርስቶስ በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም መገንባት የሚጠናቀቀውን የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ዓላማ ለመፈጸም፣ በአጽናፍ ዓለም ላይ የእግዚአብሔርን ፍርድ ለማከናወን የሚያስተውሉና የሚመረምሩ ሰባት ዓይኖች አሉት።
2. በዘካርያስ 3፥9 ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ግንባታ ሰባት ዓይኖች እንዳሉት ድንጋይ፣ እንደ የመደምደሚያው ድንጋይ (4፥7) ተተንብዮአል።
3. እነዚህ ሰባት ዓይኖች ወደ ምድር ሁሉ የተላኩት ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት ናቸው፣ ምድርን ሁሉ ይቃኛሉ—ቁ. 10።
4. በግሪኩ ሰዋሰው መሠረት፣ *እነርሱም* የሚለው አመልካች ተውላጠ ስም *ሰባት ዓይኖች* ነው—ራእ. 5፥6።
5. ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት የሚያመለክቱት የበጉን ሰባት ዓይኖች ብቻ እንጂ ሰባቱን ቀንዶቹን አይደለም።

IV. **"ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት"—1፥4፤ 3፥1፤ 4፥5፤ 5፥6፦**

ሀ. ራእይ 1፥4 በዙፋኑ ፊት ስላሉት ስለ ሰባቱ መናፍስት ይናገራል፦

1. ሰባቱ መናፍስት በራእይ 1፥4-5 ካለው ከሦስታንዱ አምላክ ጋር በእኩል ደረጃ ስለተቀመጡ ያለጥርጥር የእግዚአብሔር መንፈስ ናቸው።
2. በእግዚአብሔር አሠራር ውስጥ ሰባት የመጠናቀቅ ቁጥር ስለሆነ ሰባቱ መናፍስት በምድር ላለው ለእግዚአብሔር እንቅስቃሴ መሆን አለባቸው።
3. በውስጠ ነገርና በሕልውና የእግዚአብሔር መንፈስ አንድ ነው፤ በእግዚአብሔር አሠራር ያየለ አገልግሎትና ሥራ የእግዚአብሔር መንፈስ ሰባት እጥፍ ነው፦
   ሀ. ይህ በዘካርያስ 4፥2 ካለው መቅረዝ ጋር ተመሳሳይ ነው።
   ለ. በሕልውናው አንድ መቅረዝ ነው፣ በአገልግሎቱ ግን ሰባት መብራቶች ነው።
4. የራእይ መጽሐፍ በተጻፈበት ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ዘቅጣ ነበር፦
   ሀ. ዘመኑ ጨለማ ነበር።
   ለ. ሰባት እጥፍ ያየለው የእግዚአብሐር መንፈስ በምድር ላይ ላለው ለእግዚአብሐር እንቅስቃሴና ሥራ አስፈልጎ ነበር።

ለ. በማቴዎስ 28፥19 የሦስታንዱ አምላክ ቅደም ተከተል አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ነው፤ በራእይ 1፥4-5 ቅደም ተከተሉ ተቀይሯል፦

1. ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት በዝርዝር የተቀመጡት ሦስተኛ ሳይሆን ሁለተኛ ስፍራ ላይ ነው።
2. ይህ የሚገልጠው ሰባት እጥፍ የሆነው የእግዚአብሔር መንፈስ ያየለ አገልግሎት አስፈላጊነትን ነው።
3. ይህ ነጥብ በ2፥7፣ 11፣ 17፣ 29፤ 3፥6፣ 13፣ 22፤ 14፥13 እና 22፥17 ላይ ለመንፈስ ንግግር በተሰጠው ተደጋጋሚ አጽንኦት ተረጋግጧል።

ሐ. በሌሎች መልእክቶች መክፈቻ ላይ፣ አብና ወልድ ብቻ ተጠቅሰዋል፦

1. ከአብና ከወልድ ጸጋና ሰላም ለተቀባዮቹ ተሰጥተዋል።
2. በራእይ 1፥4-5 መንፈስ ተካትቷል፤ ከእርሱ ጸጋና ሰላም ወደ አብያተ ክርስቲያናት ተላልፏል።
3. ይህ የሚያመለክተው ለእግዚአብሔር እንቅስቃሴ የቤተ ክርስቲያንን ዝቅጠት ለመጻረር የመንፈስን ወሳኝ አስፈላጊነት ነው።

መ. ሰባቱ መናፍስት አብያተ ክርስቲያናት በእርግጥ ወደ ፊት እንዲሄዱ በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ እየሠሩ ነው።

ሠ. ዛሬ ሰባት እጥፍ የሆነውን መንፈስ፣ ያየለውን መንፈስ፣ የምለሳን መንፈስ ማየትና መለማመድ ያስፈልገናል—ቁ. 4-5።

## V. ***“መጽሐፉን ትወስድ ዘንድ ማኅተሞቹንም ትፈታ ዘንድ ይገባሃል፣ ታርደሃልና፣ በደምህም ለእግዚአብሔር ከነገድ ሁሉ ከቋንቋም ሁሉ ከወገንም ሁሉ ከሕዝብም ሁሉ ሰዎችን ዋጅተህ...እያሉ አዲስን ቅኔ ይዘምራሉ”—5፥9፦***

ሀ. እዚህ ጋር ቅኔው አዲስ ነው፣ ምክንያቱም ቅኔው የሚያወድሰው በግ ገና እንደታረደ ነበር።

ለ. በመላው አጽናፍ ዓለም የእግዚአብሔርን ኢኮኖሚ ምሥጢር ለመክፈት ክርስቶስ፣ ድል የሚነሣው አንበሳ፣ የሚቤዠው በግ እንጂ ሌላ ማንም የተገባው አይደለም፦

1. ድል እንደሚነሣው አንበሳ፣ ለእግዚአብሔር ሰይጣንን አሸንፏል።
2. እንደሚቤዠው በግ፣ ኃጢአትን አስወግዶልናል።
3. የእግዚአብሔርን ኢኮኖሚ ምሥጢር ለመግለጥና ለማከናወን ብቁ የሆነው ክርስቶስ ብቻ ነው።
4. ክርስቶስ የመለኮታዊውን ኢኮኖሚ ምሥጢር ማኅተም ለመክፈት የተገባው እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልገናል፤ ይህ ጌታ የተገባው የመሆኑ ገጽታ አጽናፍ ዓለማዊና የማይለካ ነው።
5. ክርስቶስ ውዳሴአችን የተገባው ነው፤ ሕይወታችን ሳይቀር የተገባው ነው።

© 2025 Living Stream Ministry